# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*


የካቲት 16 ቀን 2011 ዓ.ም.

## <u>ሰሞኑን በለገጣፎ ነዋሪዎች ላይ የተካሄደውን ዘረኛ የማፈናቀል አርምጃ አጥብቀን አናወግዛለን!</u>

ላለፉት 27 ዓመታት በሙሣሪያ ኃይል ሥልጣን የጨበጠው አረመኔው የወያኔ አገዛዝ አገሪቱን በነፍጥ ሕዝብን በዘርና በሃይማኖት ከፋፍሎ ዘጎችን በተለይም አማራውን ከኑሮውና ከጠቅላላ ኢኮኖሚ ተሳትፎ በማፈናቀል አገሪቱን ዜጎች ተዘዋውረው መሥራት ወደማይችሉባት ወደ ቁም አስር ቤት ቀይሯታል። ከእንግዲህ ዘረኛው የአምባገነን ቡድን ያመጣብንን መከራ መሸከም ይብቃን፤ ከዚህ በኋላ የምናጣው የለንም ብሎ ሕዝብ የፍርሃትንና የልዩነትን ግንብ አፍርሶ የወያኔን አከርካሪት በመምታት ወደ ታሪካዊ ትቢያ ሊያወርደው ጥረት በሚያደርግበት ወቅት በውጭ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎችና ሆዳም ምሁራን አሻሻጭነት ታግዘው የሕዝብን ድምፅ ሲያፍኑ የነበሩ የሌላ ቋንቋ ወያኔዎች ድምፁን ቀምተው በማስተጋባት የለውጡ መሪ ነን ብለው ለውጡን አግተው ተሰየሙበት። ብሎም የኢትዮጵያዊነትን ጭምብል የለበሰ ግለሰብ ተሹሞ ዛሬ ኢትዮጵያን በዘውግ ሸንሽኖና በዘረኝነት የታወሩ ፅንፈኞችን ሥልጣን ሰጥቶ በአማራውና በሌሎች ብሔረሰቦች ላይ ይህ ነው የማይባል ሰቆቃ እንዲፈጸም አድርጓል። ወያኔነት ኢትዮጵያ ላይ ቋንቋውን ቀይሮ ተሰየመባት።

ሰሞኑን በለገጣፎ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ለፍተው ደክመው ባፈሩት ገንዘብ የሰሯቸው ቤቶች በዘረኞቹ አመራር ትዕዛዝ ኢሰብዓዊ በሆነ መንገድ ፈርሶባቸዋል። ይኸው በዘውግ ተኮር ፖለቲካ ተጠራርቶ የተሰባሰበ የዘረኞች አመራር ለወሰደው እርምጃ የሰጠው ምክንያት ቦታው ለአረንጓዴ ፓርክ ይፈለጋል በሚል ሲሆን ፓርክ መሥራት የቀን ተቀን ኑሮውን ለመሸፈን የሚታገለውን ደሃ ነዋሪ ቤት ከማፍረስና ከህፃናት ትምህርት መጨናገፍ በልጦ እንደ ምክንያት መቅረቡ ብዙዎችን አስቆጥቷል። አዛውንት፣ ህሙማንና ህፃናት በተኙበት ቤታቸው ላያቸው ላይ ፈርሶባቸው ሜዳ ላይ ወድቀው ለረሃብ፣ ለቁርና ለአውሬ፣ ተጋልጠዋል። አዲሱ ሹም አስከብራለሁ የሚለው ያፈጠጠና ያገጠጠ "ሕገ መንግሥት" (ሕገ-አራዊት) ውጤቱ ሌላ ሳይሆን ይኸው ነው።
ከዛሬ 27 ዓመት በፊት  በኢትዮጵያዊነትና  ኢትዮጵያዊያን ላይ ጦርነት የጀመሩት ወያኔዎች ሲሆን አሁን እያስቀጠሉ ያሉትም  ወያኔዎች ናቸው። ኢህአዴግ/ወያኔ፤ ወያኔ/ኢህደግ። ስልቻ/ቀልቀሎ፣ ቀልቀሎ/ስልቻ እንዲሉ።

በተመሳሳይ ዘር ተኮር ጥቃት በዚህ ዓመት መስከረም ወር መጀመሪያ ላይ በቡራዩ፣ በከታ፣ በሳንሱሲ፣ በአሸዋ ሜዳ፣ በፊሊ ዶሮ፣ ...ወዘተ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች መገደላቸውና በርካታዎችም ለከባድና ለቀላል የአካል ጉዳት መዳረጋቸው ይታወቃል። ህፃናት ሳይቀሩ ኢሰብዓዊ የሆነ ድርጊት ተፈፅሞባቸዋል። ይህን ጥቃት በመቃወም ድምፃቸውን ያሰሙትን በሺህ የሚቆጠሩ የአዲስ አበባ ወጣቶችን ለቅመው ወስደው ሃሩር ወስጥ በተገነባ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ማሰቃየታቸው የምናስታውሰው ሲሆን አስካሁንም ያልተፈቱ እንዳሉ ግልጽ ነው።

በለገጣፎ ቤታቸው ፈርሶ መጠጊያ ያጡ ወገኖቻችን በህይወታቸው ያልጠበቁት ችግር ውስጥ የገቡ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ለተጠሙት ውሃ፣ ለተራቡት ዳቦ፤ እንዲሁም መጠለያ በማቅረብ ፈንታ


**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email [ESPIC@aol.com](mailto:ESPIC@aol.com)**
**Website [www.eprp.com](http://www.eprp.com)**

**EPRP**
**BP 30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**

የደረሰላቸው ነገር ቢኖር ጥቃቱና ውድመቱ ይቀጥላል የሚል ዛቻ ነው። ይህ ጥቃት በለገጣፎ ነዋሪዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያዊ ዜግነት ላይ መሆኑን ተረድቶና ጥቃታቸው በአገርና በወገን ላይ መሆኑን አውቆ  መነሳትና የሚከፈለውን መስዋዕትነት ሁሉ ከፍሎ መታገል የግድ ነው። እንደ ተስቦ እያሰራጬት ያለውን ዘረኝነት ከስረ መሰረቱ ነቅሎ ጥሎ አገርንና ትውልድን ማዳን ግድ ነውና ወገኖቻችን ላይ ይህን መሰል የናዚዎቹ አይነት ጥቃት ሲፈፀም የቆዳ ቀለም ትርጉም የለውምና እንነሳ። ዛሬ በለገጣፎ እያደረሱ ያሉትን ግፍና ሰቆቃ ነገ ወደ አዲስ አባባና ሌሎች አያመጡም ብሎ የሚተኛ ሰው ካለ የሩቁን ቀርቶ የቅርቡን የአገሩን ታሪክ ያልተረዳ ብቻ ነው።

መፍትሄው በአፈ ጮሌው ሹም የተዳፈነውን ትግል መቆስቆስና ማፋፋም ብሎም ዘረኛውን አገዛዝ አሰወግዶ፤ ሕዝብ የሥልጣን ምንጭ ለሚሆንበት ለሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ምሥረታ የሽግግር ሂደትን መጀመር ብቻ ነው። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትንና ማኅበራዊ ፍትህን በኢትዮጵያ ለማስፈን - አማራጩ ይኸው ብቻ ነው!  አሮጌውን ሥርዓት ለማስቀጠል ለሚሰየሙ አዳዲስ ፊቶች ማጨብጨብን ገትቶ፤ ከወሬ ተግባር እንዲሁም ከመጠምጠም መማር መቅደሙን ማስተዋል ያሻል። አገራችን በብዙ አርበኞች ልጆቿ መስውዕት ነፃነቷን ጠብቃ የኖረች ታሪካዊት አገር ነች። ዘረኞች እየተጋገዙ እንዲፈነጩባትና ሕዝባችንም የግፍ ገፈት ተቀባይ ሆኖ እንዲቀጥል ልንፈቅድ አይጠበቅም።

**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email [ESPIC@aol.com](mailto:ESPIC@aol.com)**
**Website [www.eprp.com](http://www.eprp.com)**

**EPRP**
**BP 30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**